| አንደኛ ዓመት ቁጥር 5<br>1st Year No. 5 | ሐረር ግንቦት 4 ቀን 1988<br>Harar, May 12 1996 |
| --- | --- |

# የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
# HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| ያንዱ ዋጋ 1.00 | በሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት<br>ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
| --- | --- | --- |


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር 5/1988

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

አርማ አዋጅ ቁጥር 5/ 1988 ........................................................ ገጽ 28


## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

### አርማ አዋጅ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 3 የክልሉ መንግሥት ሰንደቅ ዓላማና አርማ የተደነገገ መሆኑን በመገንዘብ፣

በሐረሪ ሕዝብ ክልል ሕገ-መንግሥት መሠረት የክልሉን ዓርማ የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮችን በሕግ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26/1/ሀ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አርማ አዋጅ ቁጥር 5/1988" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ክፍል አንድ
### ስለ ክልሉ ዓርማ

**2. የዓርማው ትርጉም**

1. **እርግብ**፦
የሠላም ምልክት ናት፣በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልል ሠላምና ዲሞክራሲ የሰፈነ መሆኑን ታበስራለች።

2. **ሚዛን**፦
የሐረሪ ሕዝብና የክልሉ መንግሥት ለዲሞክራሲ፣ ለፍትህና እኩልነት ያለውን ጽኑ ዓላማ ያመለክታል።

3. **ጁገል**፦
ከክልሉ ታሪክና የባህል ቅርሶች ውስጥ ዋነኛ ስለሆነ የምንንከባከበው ቅርስ መሆኑን ያመለክታል።

4. **ሞፈርናቀንበር**፦
የክልሉ ሕዝብ የልማት መርሀ-ግብርን በሥራ ላይ ለማዋል ገጠርን ማዕከል በማድረግ ለልማት ታጥቆ መነሳቱን ያመለክታል።

5. <u>የፀኃይ ጮራ፦</u>

በክልሉ ውስጥ ዕውቀትን ለማስፋፋት ብሩህ ተስፋ መኖሩን ያሳያል።

6. <u>መዘውር፦</u>

የክልሉሕዝብ ለቴክኖሎጂ ዕድገት ያለውን ፍላጎት ያመለክታል።

7. <u>የስንዴ ዘለላ፦</u>

ክልሉ በምግብ ሰብል ራሱን ለመቻል ያለውን ዓላማ ያሳያል።

8. <u>ቡና፦</u>

የሐረር ቡና ለክልሉ የውጭ ምንዛሬ እድገት ያለውን አስተዋጽኦ ያመለክታል።

3. <u>የዓርማው ስእላዊ ምስል</u>

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አርማ ስእላዊ መልክ እንደሚከተለው ነው።

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

4. <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ይህ አዋጅ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

5. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር ግንቦት 4ቀን 1988ዓም

አብዱላሂ እድሪስ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዚዳንት